# የመንግስት የሰብል እና መኖ ዝርያዎች መነሻ ዘር አስተዳደር መመሪያ ረቂቅ

መመሪያ ቁጥር **458/2013**

መግቢያ

የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ምርጥ ዘር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ብዙ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ መንግሥትም ይህን በመገንዘብ ለምርጥ ዘር አቅርቦት ትኩረት በመስጠት የፖሊስ ምህዳርን በማመቻቸት የተጠቃሚውን የምርጥ ዘር ተደራሽነት ለማረጋገጥ ከዝርያ ማፍለቅ እስከ ተመስከረለት ዘር ማምረት ድረስ ዘርፉ ብዙ ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል፡፡ በዝርያ መዝገብ ከተመዘገቡ የሰብልና የመኖ ዝርያዎች መካከል ከ85% በላይ የሚሆኑት የመንግስት ሃብት ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ለሰብልና መኖ ምርምር እና ለመነሻ ዘር ብዜት ትኩረት በመስጠት በመሰረተ ልማት፣ በሎጂስቲክ እና በሰው ኃይል አቅም ግንባታ ረገድ ከፍተኛ ሃብት ወጪ ሆኖ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡

ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ቢፈስም የመነሻ ዘር አቅርቦት እና ሥርጭት በተማከለ የመረጃ ልውውጥ ክፍተት፣ በአቅም ውስንነት ፣ ባልተቀናጀ ዘር ማምረትና ስርጭት፣ በጥራት ጉድለት እና ፍትሃዊ አጠቃቀም ባለመኖሩ ምክንያት ከፍተኛ ቅሬታ ከሚቀርብባቸው ግብዓቶች ዋነኛ ሆኗል፡፡ ይህ የህዝብ ሃብት ደግሞ በዘርፉ ለተሰማሩ ህጋዊ አምራቾች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እየቀረበ አይደለም፡፡ ለዚህም በዋናነት የሚጠቀሰው ለተፈላጊ የሰብልና የመኖ ዝርያዎች በሚፈለገው መጠንና ጥራት የመነሻ ዘር ተባዝቶ ያለመገኘቱ በግምባር ቀደምትነት ይጠቀሳል፡፡ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት እና አገር አቀፍ የሆነ የመነሻ ዘር አቅርቦት አቅምን ለመገንባት የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመርያ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አውጭው ባለሥልጣን

   የግብርና ሚኒስቴር ስለ ዕፅዋት ዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር 782/2005 በአንቀፅ 27/2 በተሰጠውሥልጣን መሰረት በአዋጁ አንቀጽ 6/3 የተደነገገውን ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ የመንግስት የሰብልና መኖ ዝርያዎች መነሻ ዘር አስተዳደር መመሪያ ቁጥር **458/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. ትርጓሜ

   3.1. ስለ ዕፅዋት ዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር 782/2005 እና የዕጽዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 375/2008 ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረጎች ትርጉም እንደተጠበቁ ሆኖ:-

3.2. "ሰብል" ማለት የብርዕ፣ የአገዳ፣ የፍራፍሬ፣ የጥራጥሬ፣ የቅባት፣ የአትክልት፣ የአኩሪት፣ የሥራሥር ሰብሎችን ነው፤

3.3. "መኖ" ማለት ቅጠሉ፣ ዘሩ፣ አገዳው፣ ሥሩ ወዘተ ክፍሎች ለእንስሳት መኖነት የሚያገለግል እጽዋት ነው፤

3.4. "በመንግስት የተለቀቁ ዝርያዎች" ማለት በፌደራል እና በክልል የመንግስት የግብርና ምርምር እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባለቤትነት በዝርያ መዝገብ የተመዘገቡ ሰብልና መኖ ዝርያዎች ናቸው፤

3.5. "መነሻ ዘር" ማለት የአራቢ፣ ቅድመ-መሥራችና መሥራች የዘር ትውልዶች ናቸው።

3.6. "ባለስልጣን" ማለት የዝርያን እና ዘር ጥራትን ለመቆጣጠር ህጋዊ ሥልጣን የተሰጠው የፌደራል ወይም የክልል መንግስታዊ ተቋም ነው።

3.7. "የብቃት ማረጋገጫ" ማለት ከባለስልጣኑ የእጽዋት ዘር እንዲያመርትና እንዲሸጥ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ለዘር አምራች የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው።

3.8. "የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ሰው" ከባለስልጣኑ የእጽዋት ዘር እንዲያመርት እና እንዲሸጥ ፈቃድ የተሰጠው ነው።

3.9. "ውል ሰጪ"ማለት መነሻ ዘር እንዲባዛለት የሚጠይቅና ከተባዛ በኋላ የሚረከብ ሰው ነው።

3.10. "ውል ተቀባይ" ማለት መነሻ ዘርን የሚያባዛ ሰው ነው።

3.11. "ቢሮ" ማለት በክልል ደረጃ ግብርናን የሚመራ መንግስታዊ ተቋም–ነው፤

3.12. "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው።

3.13. "ምርምር ተቋማት" ማለት በፌደራልና በክልል መንግስታት የሚተዳደሩ የምርምር ማዕከላት እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ነው።

3.14. "የመነሻ ዘር አምራች" ማለት ከባለስልጣኑ የማምረት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (አራቢ ዘርን ሳያካትት) የተሰጠው ሰው ነው።

4. የተፈጻሚነት ወሰን

4.1. ስለ ዕጽዋት ዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 782/2005 እና የዕጽዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 375/2008 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

4.1.1. በመደበኛው የዘር ሥርዓትና ጥራቱ በተገለጸ የዘር ሥርዓት የዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገቡና የዘር ጥራት ደረጃ የወጣላቸው ሰብሎችና መኖ ዝርያዎች መነሻ ዘር ላይ፤

4.1.2. በመንግስት ምርምር ተቋማት ባለቤትነት ሥር በተመዘገቡ ዝርያዎች፤

4.1.3. የዘር ጥራት እንዲያረጋግጥ ህጋዊ ዕውቅና ባለው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የጥራት ማረጋገጫ በተሰጠው ቅድመ መስራች እና መስራች ዘር፤

4.1.4. በምርምር ተቋማት የውስጥ ዘር ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት /የመስክና የላቦራቶሪን አካቶ/ ጥራቱ በተረጋገጠ አራቢ ዘር ላይ ነው።

4.2. ከላይ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4.1 የተገለጸው ጠቅላላ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆንባቸው፡-

4.2.1. ከአገሪቱ የዝርያ መዝገብ ውስጥ እንዲሰረዙ በተወሰነባቸው የመንግስት ተቋማት ዝርያዎች ላይ፤

4.2.2. በግል የዘር ኩባንያዎች ስም በተመዘገቡ ዝርያዎች፤

4.2.3. በዩኒየኖች ወይም በመሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት ስም በተመዘገቡ ዝርያዎች፤

4.2.4. በመንግስት የልማት ድርጅቶች ስም በተመዘገቡ ዝርያዎች ላይ ነው።

5. የመመሪያው ዓላማ

5.1. በመንግስት ምርምር ተቋማት በባለቤትነት የተመዘገቡ የሰብል እና የመኖ ዝርያዎች አቅርቦትና ሥርጭት በዕቅድ መምራትና ፍትሃዊ የሆነ አጠቃቀምን በዘላቂነት ማረጋገጥ፤

5.2. መነሻ ዘር እንዲባዛለት የሚፈልገውና አባዥው አካል በቀጥታ የሚያገናኝ በውል ላይ የተመሰረተ እና ተጠያቂነት ያለበት የመነሻ ዘር አቅርቦትና ሥርጭት ሥርዓት መዘርጋት፤

5.3. የተማከለ አገራዊ የመነሻ ዘር መረጃ ቋት ሥርዓት መዘርጋት፤

## ክፍል ሁለት

## የመነሻ ዘር ዕቅድ ዝግጅት

6. ከክልሎች የተመሰከረለት ዘር ፍላጎት በመነሳት እና ክልሎችን በማማከር የግብርና ሚኒስቴር አገራዊ የመነሻ ዘር ዕቅድን ያዘጋጃል፤

7. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ዘር አምራች

7.1. እንደተመዘገበበት አስተዳደር እርከን /ክልል ወይም ፌደራል/ የሚያመርተውን የተመሰከረለት ዘር ዕቅድ ለቢሮ ወይም ለሚኒስቴሩ ያሳውቃል፤

7.2. ቢሮ ወይም ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው የዘር እቅድ መድረክ ይሳተፋል።

7.3. ለቢሮ ወይም ለሚኒስቴሩ በቂ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "7.1" እና "7.2" ተፈጻሚ የማያደርግ ዘር አምራች የመንግስት ዝርያዎችን መነሻ ዘር እንዳይጠቀም ሊከለከል ይችላል።

8. የመነሻ ዘር ዕቅድ ዝግጅት የተመሰከረለት ዘር ከሚፈለግበት 3 ዓመት በፊት ይከናወናል።

9. በአንቀጽ 8 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቅዱ በየዓመቱ የሚከለስ ይሆናል።

10. በዕቅድ ወቅት የመነሻ ዘር ብዜት አቅም እጥረት እንዳለ ሲታመን እጥረቱ በተከሰተባቸው ሰብሎች/ዝርያዎች የማባዛት ኃለፊነት አቅም ላለው የመነሻ ዘር አምራች በውል ይሰጣል።

11. በአገር አቀፍ ደረጃ የቀጣዩ ምርት ዘመን የመነሻ ዘር ዕቅድ ዝግጅት በዓመት አንድ ጊዜ የሚከናወን ሆኖ ከታህሳስ በፊት መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሶስት

## በውል ላይ የተመሰረተ የመነሻ ዘር ብዜት አፈጻጸም

12. የመነሻ ዘር ማምረት የብቃት ማረጋገጫ ባገኙ አምራቾች መካከል በውል ተመስርቶ ይካሄዳል፡፡

13. ውል ተቀባዩች

13.1. በውል ሰጪዎች ተመስርተው ለሚያቅዱት መነሻ ዘር ብዜትና ሥርጭት ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ፤

13.2. ከዕቅዳቸው ውጭ በቢሮው ወይም በሚኒስቴሩ ተጨማሪ እንዲያመርቱ ሲጠየቁ ግብርና ሚኒስቴር ወይንም ክልል ቢሮ ውል ሰጪ ሆኖ እንዲመረት ያስደርጋሉ፡፡

14. የመንግስት የመነሻ ዘር ብዜት ሥራ ውል ቢያንስ የሚከተሉትን ጉዳዩች ያካተተ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፡፡

14.1. የኢትዮጵያ ዘር ጥራት ደራጃዎች ያካተተ፤

14.2. የሚረካከቡት የትውልድ ደረጃ፤ዘር መጠን፤

14.3. ስለ ክፍያ ሁኔታ፤

14.4. የርክክብ ጊዜና ቦታ፤

14.5. ውል ስለ ማቋረጥ፤

14.6. ውሉ ስለማይጸናባቸው ጉዳዮች፤

14.7. ያለ መግባባትን መፍታት/ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት፤

14.8. ከአቅም በላይ በሆነ መንገድ የሚደርስን አደጋ ስለማሳወቅ

14.9. ሌሎች ተጓዳኝ ጉዳዮች

## ክፍል አራት

## የመነሻ ዘር ሥርጭት አፈጻጸም

15. የመነሻ ዘር ሥርጭት ሚኒስቴሩ ባዘጋጀው የመረጃ ቋት እና በውሎች ላይ ተመስርቶ ፍትሃዊ ሥርጭት መኖሩ በቢሮ ለክልል ወይም በሚኒስቴሩ /ለአገር አቀፍ ሥርጭት/ ሲረጋገጥ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

16. የማንኛውንም ሰብል እና የመኖ የመንግስት ዝርያዎችን መነሻ ዘር የብቃት ማረጋገጫ ላልተሠጠው ዘር አምራች ማሰራጨት አይቻልም፡፡

17. የተመረተው የመነሻ ዘር ከአገሪቱ ፍላጎት በላይ መሆኑ በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ

17.1. በቅድሚያ ለመጠባበቂያ ዘር ክምችት አስተዳደር እንዲውል ይደረጋል፤

፩/ ዘር አምራች ድርጅቱ ቢያንስ በዓመቱ ካመረተው 20 በመቶ ያህሉን በራሱ መጋዘን በመጠባበቂያነት እንዲያውል ይደረጋል፤

፪/ በንኡስ አንቀጽ 17.1/፩/ ሥር በተመላከተው መሰረት ከአምራቹ በላይ የሆነውን የግብርና ሚኒስቴር በሚዘረጋው የመጠባበቂያ ዘር ክምችት መጋዘኖች እንዲከማች ያደርጋል።

17.2. ከመጠባበቂያ ዘር ክምችት ፍላጎት በላይ የሆነውን ለእህል አምራቾች በተመሰከረለት ዘር ደረጃ መሸጥ ይቻላል።

18. ውል የገባው ዘር አምራች ስምምነት ላይ በተደረሰበት የጊዜ ገደብ ቀርቦ ዘሩን ካላነሳ የመነሻ ዘር አቅራቢው በውሉ በተወሰነው የጊዜ ገደብ መሰረት

18.1. መነሻ ዘሩን የብቃት ማረጋገጫ ላለው ሌላ ዘር አምራች ማሰራጨት ይችላል።

18.2. ውል ሰጪው ውሉን በማፍረሱ ውል ተቀባዩ መብቱን በድርድር ወይም በፍርድ ቤት ይጠይቃል።

19. በተወሰኑ ሰብሎች የመነሻ ዘር እጥረት በተፈለገው መጠን እንደሌለ ሲረጋገጥ

19.1. ሚኒስቴሩ በዓመቱ የተገኘውን መነሻ ዘር በሙሉ አቅም ላላቸው ዘር አምራቾች ለመነሻ ዘር ብዜት አገልግሎት እንዲሰራጭ ማዘዝ ይችላል።

19.2. አቅም ያለው ዘር አምራቾች በሚከተለው መስፈርት መሠረት ይለያል፤

፩/ ተቋሙ ለዓመቱ የያዘው ዕቅድ፤

፪/ የተጠናከረ የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት፤

፫/ የማሳው ሥነ-ምህዳር ለሰብሉ ተስማሚ መሆኑ፤

፬// የአምራቹ የማሳ መጠን፤

፭/ የእርሻ መሣሪያዎች አቅም፤

፮/ በቂ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል/ባለሙያ ያለው ስለመሆኑ፤

፯/ ለሌሎች አምራቾች የማቅረብ አቅም፤

20. አባዥ ያጡ የሰብልና መኖ ዝርያ መነሻ ዘር ብዜትን በተመለከተ የምርምር ተቋማት ከሚኒሲቴሩ ወይም ከቢሮዎች ጋር በሚያደርጉት ምክክርና በሚደርሱበት ስምምነት መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል አምስት

**ዝርያን ስለማስተዋወቅ**

21. በመንግስት የምርምር ተቋም ስም የተመዘገበን የሰብልና የመኖ ዝርያ የሚጠቀም ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ሰው፡-

21.1. የተመዘገቡ ዝርያዎችን ለአርሶ/አርብቶ አደሮች የማስተዋወቅ ግዴታ በማሳ፣ በብዙሃን መገናኛ፣ በበራሪ ወረቀት ወዘተ ይኖርበታል።

21.2. ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ቢያንስ 0.5% ያህሉን ለዝርያዎች ማስተዋወቅ ይመድባል፡፡

21.3. የዝርያ ማስተዋወቁን ሥራ ተግባራዊ ሲያደርግ፡-

ሀ/ከታቀደበት ጊዜ ቢያንስ ከ 3 ዓመት በፊት ጀምሮ የተለቀቁ ዝርዎችን፤

ለ/ ማህበራዊ ግጼታንም ከመወጣት አንጻር የማስተዋወቅ ሥራው የገበያ ፍላጎት ካልተፈጠረላቸው ዝርያዎችም ያካተተ መሆን አለበት፡፡

22. በቅድመ-መስራች እና መስራች ደረጃ ያለን የመንግስት ዝርያ በአንድ ክልል በሚገኝ አርሶአደር ማሳ ከማስተዋወቅ በፊት

22.1. ቢሮው፣ የክልሉ ግብርና ምርምር ኢንስቲቱት እና የማስተዋወቁ ሥራ የሚካሄድበት የአርሶአደሮች ማሰልጠኛ ማዕከል በጋራ ዕቅዳቸው የያዙት መሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

22.2. ዝርያ የማስተዋወቁ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠው ዘር አምራች ጋር ትስስር የተደረገለት መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

**ሚኒስቴሩ፡-**

23. በዘር አምራቾች የሚካሄደውን የማስተዋወቅ ሥራ በዕቅድ መመራቱን ይከታተላል፡፡

24. ከቢሮዎች የተመሰከረለት ዘር ዕቅድ በመነሳት

24.1. የ 3 ዓመት አገራዊ የመነሻ ዘር ማምረት ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡

24.2. በየዓመቱ የሚካሄደውን የዕቅድ ክለሳ ሥራ ያስተባብራል፡፡

24.3. አምራቾች እንደደረሱበት አቅምና በተቋቋሙበት የምስረታ ደንብ/አዋጅ በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት የመነሻ ዘር ማምረት ዕቅድን ይደለድላል፡፡ አመራረቱንም ይከታተላል፡፡

25. የመነሻ ዘር ዕቅድ ዝግጅት እና አፈጻጸምንም የሚመራ፣ የሚያስተባብር እና የሚገመግም አካል ያደራጃል፤ ይሰይማል፡፡

26. በውል ላይ የመነሻ ዘር ማምረትን በተመለከተ

26.1. የማዋዋል ሥራ ይሰራል፤

26.2. አለመግባባቶች ወይም ቅሬታዎች ሲከሰቱ በአስተዳደር የሚፈቱበት ሁኔታ ያመቻቻል፤

26.3. አገራዊ ውሎችን መዝግቦ ይይዛል፡፡

26.4. በውሎች መሰረት አለመግባባቶች በድርድር የማይፈቱበት ደረጃ ላይ ሲደረስ በፍርድ ቤት አስረጅ ሆኖ ይቀርባል፤

27. የመነሻ ዘር በማዕከላዊ የመረጃ ቋት እንዲመራ ያደርጋል፤ተገቢውን ሥርዓትም ይዘረጋል፡፡

28. በፌዴራል ወይንም በክልል ለሚተዳደሩ የመንግስት መነሻ ዘር አምራች ማዕከላት ለሥራው የሚመጥን በጀት መመደቡን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

ቢሮ፡-

29. አገራዊ የዘር ማምረት ግብን መሰረት በማድረግና የክልሉን አምራቾች በማስተባበር የተመሰከረለት ዘር ፍላጎት በሰብል፣በመኖ እና በዝርያ ዓይነት በመለየት ከአገራዊው የመነሻ ዘር ዕቅድ አንድ ወር ቀድሞ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀርባል፡፡

30. በክልል ደረጃ በመነሻ ዘር አቅርቦት ራስን የሚያስችል አቅም እንዲገነባ ያደርጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ፡-

30.1. የአምስት ዓመት ጠቋሚ እቅድ ያዘጋጃል፡፡

30.2. የሚዘጋጀው ዕቅድ በጥቂቱ የሚከተለው ይዘት ይኖረዋል፡፡

፩/ የዘር ማምረቱን የሚመራ የእርሻ ክፍል አደረጃጀት፤

፪/ ለመነሻ ዘር አምራቾች በባለቤትነት የሚሰጥ ማሳ መጠን፤

፫/ በየዓመቱ የሚፈለግ የአራቢ ዘር መጠንና የሚገኝበት የምርምር ማዕከል፤

፬/ የአራቢ ዘሩን በጥራት ለመያዝ የሚያስችል የዝርያ ማደስ (breeding maintenance) አደረጃጀትና የባለሙያ አመዳደብ፤

፭/ ከአራቢው ዘር ባለቤት ማዕከል ጋር ቀጣይነት ያለው የአራቢ ዘር አቅርቦት ትስስር ስለመፈጠሩ የሚያመለክት የአሰራር ውል፤

31. ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ የሚያሳውቀውን ዕቅድ በአገራዊ የዕቅድ ዝግጅት ቀርቦ ያስረዳል፤ እንደአስፈላጊነቱ በሚሰጠው አስተያየት መሰረትም ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል፤

32. በክልል ደረጃ የመነሻ ዘርን በኃላፊነት የሚመራና የሚያስተባብር አካል ያደራጃል፤ ይሰይማል፤

33. በክልል ደረጃ ለመነሻ ዘር ብዜት የሚያስፈለግ በጀት ለምርምር ማዕከላት ከመንግስት ፋይናንስ መመደቡን ይከታተላል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የበጀት ድጋፍ ያደርጋል፤

34. አገራዊው ዕቅድ ተፈጻሚ እንዲሆን ከሚኒስቴሩ ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

## የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክርቤት

35. ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው አገራዊ ዕቅድ ዝግጅት ይሳተፋል፤

36. ለዘር ብዜት ሥራ የሚያስፈልግ ተጨማሪ ሃብት ያፈላልጋል፤ ሲገኝም እንደየሥራው ሥፋት ለመነሻ ዘር አባዥ ይደለድላል፤

37. የምርምር ተቋማት የመነሻ ዘር ማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ይሰራል፤

## የመንግስት መነሻ ዘር አምራቾች

38. የመነሻ ዘር ብዜት ዕቅድን መሰረት በማድረግ፡-

38.1. በአድራሻ ተለይቶ የተሰጣቸውን መነሻ ዘር ለማምረት ከተመሰከረለት ዘር አምራቾች ጋር ውል ያስራሉ፤

38.2. በገቡት ውል መሰረት አገሪቱ ያጸደቀቻቸውን እና የተቀበለቻቸውን ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና የጥራት መስፈርቶች መሰረት በማድረግ መነሻ ዘር ያመርታሉ፤

38.3. ያመረቱት ዘር ጥራቱን ጠብቆ ስለመመረቱ፣ ስለመዘጋጀቱና ስለመታሸጉ በባለስልጣን ሲረጋገጥ ከውል ሰጪው ጋር በገቡት ውል መሰረት ያስረክባሉ፡፡

38.4. ውል ሰጪው በገባው ውል በተወሰነው ማንሻ ጊዜ መነሻ ዘሩን የማያነሳ ከሆነ

38.4.1. ውል ላሰረ ወይም ላላሰረ ነገር ግን የብቃት ማረጋገጫ ለተሰጠው ዘር አምራች ማስረጫት ይችላሉ፡፡

38.4.2. የቀረበው መነሻ ዘር ከአገራዊ ፍላጎት ባለይ ከሆነ ከሚኒስቴሩ ወይም ከክልል ቢሮዎች ጋር በመመካከር ያስረክባል፡፡

38.4.3. ሌሎች ህጋዊ መብቶቻቸውን በኢትዮጵያ የውል ህግ መሰረት ያስከብራሉ፡፡

**የተመሰከረለት ዘር አምራቾች**

39. የብቃት ማረጋገጫ እንዳገኙበት የአስተዳደር የሥራ ክልል የተመከረለትና የመነሻ ዘር ፍላጎታቸውን ለቢሮ ወይም ለሚኒስቴሩ ከአገራዊው ዕቅድ አንድ ወር ቀድመው ያሳውቃሉ፤

40. በጽሁፍ ካሳወቁ በኋላ ቢሮው ወይም ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው ክልላዊ ወይም አገራዊ የእቅድ ዝግጅት ሳምንት ይሳተፋሉ፤

41. በጸደቀው ዕቅድ መሠረት በአድራሻቸው የተመላከተውን የመነሻ ዘር ለማስመረት ከመነሻ ዘር አምራቾች ጋር ውል ያስራሉ፤

42. በውሉም መሰረት የጠየቁትን መነሻ ዘር ተገቢውን ክፍያ ከፍለው በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ያነሳሉ፤

43. ውል ተቀባዩ ውል የገባበትን መነሻ ዘር ማቅረብ ካልቻለ ጉዳዩን በቢሮዎች ወይም በሚኒስቴሩ በድርድር ወይም በፍርድ ቤት እንዲፈታ ማድረግ ይችላሉ፡፡

## ክፍልሰባት

## ስለቅሬታ አቀራረብ እና ሌሎች ድንጋጌዎች

44. ስለ ዕፅዋት ዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 25 ፣ስለ ዕጽዋት ዘር የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 361/2008 እና በዚህ መመሪያ መሠረት በመንግስት የልማት ዘርዎች መነሻ ዘር አጠቃቀም ላይ ቅሬታ ያለው ሰው

44.1. ቅሬታው በፌደራል የብቃት ማረጋገጫ ካገኘ ውል ሰጪ/ተቀባይ ጋር ከሆነ ቅሬታውን ለሚኒስቴሩ ወይም

44.2. ቅሬታው በክልል የብቃት ማረጋገጫ ካገኘ ውል ሰጪ/ተቀባይ ጋር ከሆነ ቅሬታውን ለቢሮ ማቅረብ ይችላል፤

45. ቅሬታ የቀረበለት ሚኒስቴር ወይም ቢሮ ስለዕጽዋት ዘር በወጣው አዋጅ 782/2005 በተጠቀሰው ጊዜ መሰረት ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።

46. ሚኒስቴሩ ወይም ቢሮው ዘር አምራቹ የእጽዋት ዘር አዋጁን፣ ደንቦችን እና ይህን መመሪያ ጥሶ ሲገኝ፤

46.1. በአስተዳደራዊ ውሳኔ የመንግስትን ዝርያዎች እንዳይጠቀም እና የመነሻ ዘርም እንዳያገኝ ያደርጋል፤

46.2. ዘር ለማምረት የተሰጠውን የማምረት ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያግዳል፣ እንደአስፈላጊነቱም ይሰርዛል፤

46.3. የወንጀል ጥርጣሬ ካለም በህግ ተጠያቂ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

## ክፍል ሰምንት

## መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

47. ይህ መመሪያ ከግንቦት22ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**ዑመር ሁሴን**

**ግብርናና ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**